ሳምንታዊ ዜና (መስከረም 17 ቀን 2001 ዓ. ም.)

አዲስ አበባ በፌዴራል ፖሊስ ጥብቅ ጥበቃ ስር ገባች፤ ቤተ-መንግስቱ መለስ ወደ ኒውዮርክ ከሄደ ጀምሮ በ3 ዙር ጥበቃ ተወጥሮዋል፤ ሳሞራ የኑስ ውሎው ቤተ- መንግስት ሆኖዋል ተባለ፤ ወያኔ ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ከፍተኛ ባለስልጣኖቹን ከስራ አስፈፃሚነት አባረረ፤ የፌዴራል ፖሊስ የአዋሳን ከተማ ነዋሪዎች ሲያዋክቡ ሰነበቱ፤ የአዋሳ ከተማ ፖሊሶች ትጥቅ ፈትተው እንደነበር ተጋለጠ፤ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በመለስ ድርጊት ተበሳጭተው የአራት ግብዣ ላይ ሳይገኙ ቀሩ፤ ረሀቡ አሁንም እጅግ አስፈሪ በሆነ መልኩ እየተስፋፋ -እነ መለስ እያሾፉ መሆናቸው ዲፕሎማቶችን አሳዘነ፤ በጎንደር ውስጥ በወያኔ ጦር እና በባለስልጣን አጃቢ ታጣቂዎች መሀል በተነሳ ተኩስ 7 ሰዎች ተገደሉ- ባለስልጣኑም ቆሰለ፤ ህዝቡ በወያኔ ወታደሮች እንግልትና ወከባ እየደረሰበት ነው፤ በየመስሪያ ቤቱ ሰራተኛውን የሚሰልሉ አምስት አምስት የወያኔ ካድሬዎች ተመደቡ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያዳምጡ ………………..

በአዲስ አበባ ከተማ ከማክሰኞ መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ከወትሮው በተለየ መልኩ ጥብቅ ጥበቃ እየተደረገ መሆኑን ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን ገለፀ::

በቲዮታ ፒክ አፕ መኪና ላይ መትረየስ ተጠምዶ የፌዴራል ፖሊሶች ከወትሮው በተለየ መልኩ በአዲስ አበባ ዋና ዋና አደባባዮች እየተዘዋወሩ ጥበቃ እያደረጉ መሆኑን የገለፀው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን እግረኛ የፌዴራል ፖሊሶችም ከነሙሉ ትጥቃቸው ተበትነው ጥብቅ ጥበቃ እያደረጉ መሆኑን ገልፆዋል::

ከዚህ ቀደም ጥብቅ ጥበቃ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲደረግ የነበረ ቢሆንም የሰሞኑ ጥበቃ ግን የፌዴራል ፖሊሶቹ ሙሉ ትጥቅ አንግበው በአንድ ላይ አራት እና ከዛም በላይ ሆነው እየተዘዋወሩ ከመሆናቸውም ባሻገር በየጉራንጉሩ እየገቡ በየሰፈር ውስጥ የተቀመጡ ወጣቶችን ጭምር እያስፈራሩ እና ድልድይ ላይ ተቀምጠው እንደሚውሉ ዘገባው አስረድቶዋል::

ጥበቃው የተጠናከረው የደመራን በዓል ምክንያት በማድረግ አደጋ ጣይ ኃይሎች ወደ ከተማቀዋ ሰርገው ይገባሉ ተብሎ ሳይሆን እንዳልቀረ ግምታቸውን የሚሰነዝሩት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ከሳምንት በፊት የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ አደጋ ሊጣል ይችላል ተብሎ በመረጃና ደህንነት ባለስልጣናት ዘንድ ከፍተኛ ስጋት ተፈጥሮ እራሳቸው ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣናቱ ለበታቾቻቸው ሳይነግሩና ሳያማክሩ በጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርተው እንደነበረ ዘገባው አስታውሶ አሁንም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ይሁን በሌላ ምክንያት አዲስ አበባ ከተማ በፌዴራል ፖሊስ የስንግ ተይዛ መሰንበቱዋ ታውቀዋል::

ከመስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ አዲስ አበባ በፌዴራል ፖሊስ የስንግ ተወጥራ ባለበት ወቅት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ወደ ውጭ ሀገር ለስብሰባ ተብሎ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ቤተ-መንግስቱም ከወትሮው በተለየ መልኩ በጥብቅ ጥበቃ ስር እንዳለ የቤተ- መንግስት ምንጮች ገለፁ::

በ3 ዙር የሚጠበቀው የመለስ መኖሪያ ቤተ-መንግስት ከውስጥ በኩል በቅርቡ በድብቅ የገቡት የወልቃይት ተወላጅ ወታደሮች እንደሆኑ የገለፁት ምንጮቹ በሁለተኛው ዙር ያሉት ወታደሮች የትግራይ ተወላጆች ብቻ እና የመጨረሻው 3ኛ ዙር ግን ከህዝቡ ጋር በቀላሉ የሚገናኙ ከሁሉም የሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰብ የተውጣጡ መሆናቸውን ምንጮቹ አስረድተዋል::

በአሁን ወቅት ቤተ- መንግስቱ በጥብቅ ጥበቃ ስር ሊገባ የቻለው በወያኔ ባለስልጣናት መካከል ውስጥ ወስጡን ሽኩቻቸው እያየለ በመምጣቱ የተነሳ መለስና ባለቤቱ አዜብ እንዲሁም የነሱ ጀሌዎች መፈንቅለ መንግስት ሊደረግ ይችላል በሚል የዘወትር ቅዠት ውስጣቸው ስላለ በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ያሉት ምንጮቹ መለስ ወደ ውጭ ከሄደ ቀን ጀምሮ ሳሞራ የኑስ ሲቪል ለብሶ ረጅም ሰዓት በቤተ መንግስት ግቢ ውስጥ እንደሚያሳልፍ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በህዝብ እንባና ደም ሲቀልዱ የኖሩት እና አሁንም እየቀለዱ ያሉት መለስና ባለቤቱ ባደረባቸው ውስጣዊ ስጋት የአዜብ ሀገር ተወላጅ የሆኑ አንድ ሻለቃ ወታደሮች በድብቅ አሰልጥነው ያስገቡ ቢሆንም እንዲህም ሆኖ ባልና ሚስቱ እረፍት ሊያገኙ እንዳልቻሉም ምንጮቹ አስረድተዋል::

ሁልጊዜም በስጋትና በፍርት ህዝብ ያምፅብናል የሚሉት የወያኔ ባለስልጣናት ከ400 ሺህ በላይ የታጠቀ ኃይል በሀገሪቱ አሰማርተው መልሰው ጦሩንም መጠርጠራቸው አስገራሚ ነው ሲሉ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

እንደ ሸንኮራ አገዳ መጥጦ መጣል የሚያውቅበት ወያኔ ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ባለስልጣናት ከፓርቲ ስልጣናቸው ማንሳቱ ታወቀ::

እንደ ገደል ማሚቶ መለስ ያለውን ብቻ ሲያስተጋቡ የነበሩት እነዚሁ ተባራሪ ሆድ አደር ባለስልጣናት ከሶስቱም የወያኔ ተቀፅላ ድርጅት ውስጥ ሲሆኑ ከኦህዴድ ሽፈራው ጃርሶ የተባለው ቀድሞ የውሀ ሀብት ሚኒስትር የነበረውና በአሁኑ ወቅት የተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ ሆኖ እያገለገለ የሚገኝ ሲሆን ፤ከኦህዴድ ስራ አስፈፃሚ ተባርሮ በምትኩ የገንዘብ ሚኒስትሩ ሱፍያን አህመድ የተባለው ሌላው የወያኔ ካድሬ የተተካ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን ሽፈራው ጃርሶ ከስራ አስፈጻሚነት የተነሳው ከዚህ ቀደም በተደረጉ ግምገማዎች ነው ያሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በተለይም በ1996 መጨረሻ ላይ በተደረገው የአጠቃላይ ግምገማ ላይ መለስ ዜናዊ ኦህዴድ የተባሉትን ባለስልጣናት «እናንተ ጀርባችሁ ቢፈተሽ ኦነግ ነው» በማለት ሲናገር ሽፈራው ጃርሶ በበኩሉ «እናንተም ጀርባችሁ ቢፈተሽ ሻዕቢያ ነው» በማለት ድፍረት የተሞላበት ምላሽ በመስጠቱ ከነበረበት የውሀ ሀብት ሚኒስትርት እንዲነሳ የተደረገ መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ አሁንም በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የመንግስት ተጠሪ በሚል ያስቀመጡት ሲሆን በቅርቡ የምክር ቤት አቀማመጥ ተብሎ በተደለደለው መሰረት ሲኒየር እሱ የነበረ ቢሆንም ቀስ በቀስ ስልጣኑን

ለማሳጣት ሲባል ግርማ ብሩ የሸፈራውን ቦታ እንዲይዝ መደረጉን ያስታወሱት ምንጮች ምናልባትም ፓርላማ ሲከፈት ከምክር ቤት ተጠሪነቱ ቦታ ሊያነሱት ይችላሉ ይህ ደግሞ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ምን ያህል ቂም ቋዋጥሮ እንደሚሄድ ያሳያል ሲሉ አብራርተዋል::

ደኢህዴን የተባለው ሌላው የወያኔ ተቀፅላ ድርጅት በበኩሉ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስትር ካሱ ኢላላን ፤የሴቶች ጉዳይ ሚኒስትር ወ/ሮ ሂሩት ዴሌቦን ፤የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሲራጅ ፈርጌሳን ከስራ አስፈፃሚነት ያሰናበተ ሲሆን የክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት ፀጋዬ ማሞ ደግሞ ከምክትል ፕሬዝደንትነቱም ጭምር የተባረረ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ሌሎች የደኢህዴን የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ባለስልጣን የነበሩ ካይዳኪ ገዘሸኝ እና ሙፈሪት ከሚል የተባሉትን ከነበሩበት የፓርቲ ስልጣናቸው የተባረሩ መሆኑንም ጨምሮ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

የመለስ ቀኝ እጅ ነው የሚባልለትና « ከነፈሰው የማነፍስ»ተብሎ ከመለስ ውደሳ የተሰጠው አዲሱ ለገሰ የሚመራው ብአዴን የተባለው ሌላው ተለጣፊ ድርጅትም ህላዊ ዮሴፍን ፤የክልሉ ፕሬዝዳንት የነበረውና በአያሌው ጎበዜ የተተካው ዮሴፍ ፍረታን፤ የክልሉ ባለስልጣን ነበሩትን ዮሐንስ ቡዋያለው እና አምባቸው መኮንንን ከስራ አስፈፃሚነት ያባረራቸው ሲሆን ተፈራ ዋልዋን ደግሞ ከምክትል ሊቀ መንበርነት ያባረሩት መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ወጣት ካድሬዎችን በአዲስ መልክ መተካት የሚል መርህ በቃል ብቻ ይዞ የተጉዋዘው የወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ 39 የስራ አስፈፃሚና 180 የማዕከላዊ ኮሚተ አባላት ያሉት ሲሆን ፤ከዚህ ውስጥ አንድም ወጣት ካድሬ ያላስገባ መሆኑን ገለፀው ይኸው ዘገባ ይህንን ያደረጉት እነ መለስ በወጣት ካድሬዎቹ ላይ እምነት ስለሌላቸው እንደሆነም ጨምሮ አስረድቶዋል::

በተለይ ወጣት ካድሬዎቹ የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች እነ መለስን ፈተና ላይ እየጣላቸው በመሆኑና በመደንገጣቸው የተነሳ በቃል ብቻ ለማስመሰል ወጣቶችን እናበረታታለን ፤ ስልጣን እንዲይዙ እናደርጋለን እያሉ ይለፍፉ እንጂ በወጣት ካድሬዎቹ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ ስላላቸው አንድም እንዳይመረጡ ማድረጉን ዘገባው አብራርቶዋል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግዴታ የዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎችን አባል እያደረጉ ቢሆንም መምህሩም ተማሪውም ምንም አስተዋፅኦ ያላደረጉ በመሆናቸው እናስገድዳለን በማለት ሲያስፈራራ የከረመው በረከት ስምኦን «በተለይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የፓርቲውን መታወቂያ ስራ መፈለጊያ አደረጉት እንጂ ምንም አልጠቀሙንም» ሲል በምሬት ሲገልፅ ተደምጦዋል::

ወያኔ ባደረገው የስራ አስፈፃሚ ምርጫ ላይ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን በስራ አስፈፃሚ ውስጥ ባለመካተቱዋ ስትበሳጭና ስትናደድ እንደነበር የገለፀው ዘገባ ባለስልጣናቱን ስታመናጭቃቸው

መታየቱንም ዘገባው አጋልጦዋል:: ከስራ አስፈፃሚ ውስጥ የተካተተቸው ብቸኛዋ ሴት የኦህዴዱዋ ካድሬ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስትር ወ/ሮ አስቴር ማሞ ስትሆን «አንቺ ምን የተሻለ ስራ ሰርተሽ ነው የተመረጥሽው »እያለች አዜብ ጎላ በተደጋጋሚ ስትጠይቃት እንደነበርና ለጊዜው ምንጮቹ ስማቸውን ለመግለፅ ያልፈለጉዋቸውን ባለስልጣናት ስትሳደብ እንደነበረም ዘገባው አስረድቶዋል::

የስራ አስፈፃሚ የሚመርጠው አራቱም የወያኔ ድርጅቶች ብቻቸውን በመሆኑ አዜብ መስፍን በህወሀት ስራ አስፈፃሚነት ባለመመረጡዋ ቁጭት የገባት አዋሳ ስትደርስ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በዚህም የተነሳ በመናደዱዋ እንደ እብድ እያደረጋት ስትቆናጠር እንደነበረም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ከ20 ዓመታት በላይ የፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ ከ17 ዓመታት በላይ የመንግስት ስልጣኑን ይዞ የቆየው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ ጎላ አሱዋም እንደባልዋ የስልጣን ጥም ያሰከራት በመሆኑዋ ለምን ስራ አስፈፃሚ ውስጥ አልገባሁም እያለች ሆድ አደር የመለስ አሽከር ካድሬዎችን ስታምስ መታየቱዋ በእጅጉ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲልም ዘገባው ምንጮቹን ዋቢ አድርጎ አትቶዋል::

አዋሳ ከተማ ለ3 ቀናት በተደረገው ጉባኤ ላይ ለጥበቃ ተብሎ የፌዴራል ፖሊስና ስውር ደህንነቶች በከተማዋ ተሰማርተው ህዝቡን አላላውስ ብለው ከማስቸገራቸውም በተጨማሪ የአዋሳ ከተማ ፖሊሶችን የወያኔ ባለስልጣናት ባለማመናቸው ትጥቅ አስፈትተዋቸው ለአራት ቀናት ጀሌ አድርገዋቸው እንደሰነበቱ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የወያኔ ባለስልጣናት በአዋሳ ከተማ አቅራቢያ ሎቄ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በርካታ የሲዳማ ብሔር ተወላጆችን እንዲገደሉ ካደረጉ ወዲህ ከፍተኛ ስጋት የገባቸው እነ መለስ ዜናዊ ዘንድሮም ጉባኤው ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀረው የአዋሳ ከተማ ፖሊሶችን በመፍራት ትጥቃቸውን እንዲፈቱ በማድረግ ለ4 ተከታታይ ቀናት ባዶ እጃቸውን እንዲጠብቁ ተደርገው መሰንበታቸውን ዘገባው አስረድቶዋል::

ጉባኤው በተጠናቀቀ ማግስት መስከረም 8 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ የተነጠቁትን ትጥቅ መልሰው እንዲወስዱ ቢጠየቁም ፖሊሶቹ አሻፈረኝ በማለት «መጀመሪያም እናንተ በእኛ ላይ እምነት የላችሁም ::ስለዚህ ላላመናችሁት ፖሊስ እንዴት ትሰጣላችሁ? ለተፈፀመብን የሞራል ድቀት ካሳ ያስፈልገናል ይህ ካልተደረገልን ስራም አንገባም »በማለት የክልሉ ፕሬዝደንትና የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር የሆነውን ሽፈራው ሽጉጤን በጥያቄ ያጣደፉት ቢሆንም «ለጊዜው ስራችሁን ጀምሩና ቀስ በቀስ ያነሳችሁትን ጥያቄ እንመልሳለን »በማለት የሽንገላ መልስ የሰጣቸው ቢሆንም በርካታ የከተማዋ ፖሊሶች ግን እስከ ቅርብ ቀናት ድረስ ወደ ስራቸው ያልተመለሱ በመሆኑ የአዋሳ ከተማን የፌዴራል ፖሊስ ለመጠበቅ እንደተደረገ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

መለስ ዜናዊና ደሳለኝ ኃይለማሪያም የፌዴራል ፖሊስና አግአዚ የተባለውን ቅልብ ጦር በማዘዝ ብዙ የሲዳማ ተወላጆችን ካስጨፈጨፉ በሀዋላ የክልሉ ፖሊሶችን ለማመን ስለተቸገሩ ትጥቃቸውን

እንዲፈቱ ማድረጋቸው የሰሩት ግፍና በደል እያስደነገጣቸው ነው ያሉት አንድ የአዋሳ ከተማ ነዋሪ ዛሬ በመሳሪያ ሀይል ተከብበው ቢኮፈሱም ነገ ግን በህዝብ ደም እጃቸው የጨቀየው ባለስልጣናት ከተጠያቂነት አያመልጡም በማለት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ከስሩ ያሉትን ቅጥረኛ ፖሊሶችንና ወታደሮችን ብቻ ሳይሆን የቅርብ ሰዎች ናቸው የተባሉትን ባለስልጣናት ጭምር መለስ ዜናዊ ባለማመኑ የተነሳ ብቻውን በደህንነት ታጥሮ እንደሰነበተ የገለፀው የደረሰን ዘገባ በተለይም የጉባኤው ማጠናቀቂያ ዕለት በአዋሳ ዋቢ ሸበሌ ሆተል ለባለስልጣናቱ ግብዣ ተደርጎላቸው የነበረ ቢሆንም አዲሱ ለገሰን ጨምሮ ሌሎች የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በዋናው የሆተሉ በር እንዳይገቡ ተከልክለው በጉዋሮ በኩል እንደሰረቀ ሰው እንዲገቡ ልዩ የመለስ ጠባቂዎች በማስገደዳቸው በርካቶቹ ተናድደው በግብዣው ላይ ሳይገኙ እንደቀሩ ታውቋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሁሉንም ስልጣን በእጁ ካስገባ ወዲህ በየቀኑ ውስጡ በፈጠረው ስጋትና ፍርሀት በመወጠሩ የተነሳ በግብዣው ዕለት አስቀድሞ ወደ ሆተሉ ገብቶ ሌሎች ባለስልጣናትን በፊት ለፊት እንዳይገቡ በማስደረጉ በርካታ ባለስልጣናት እየተበሳጩ በግብዣው ላይ ሳይገኙ የቀሩ ሲሆን በዚህም መለስ በበኩሉ ባለስልጣናቱ በመቅረታቸው ምክንያት መበሳጨቱንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

ያለ አንዳች ውጤት ሲታሽና ሲታመስ የሰነበተው የወያኔ ባለስልጣናት ስብሰባና ጉባኤ ለህዝቡ አንዳችም ያመጣው ፋይዳ ካለመኖሩም በተጨማሪ የአገዛዙን እድሜ ለማራዘም ይረዳው ዘንድ አዲስ ስልት ለመንደፍ እንደነበረም የስብሰባውን ሂደት የተከታተሉ ምንጮች ገልፀዋል።

መቀሌ ፤ባህር ዳር ፤አርሲ ፤ወላይታ ሶዶ ፤በመጨረሻም አዋሳ ከተማ የወያኔ ባለስልጣናት ስብሰባና ጉባኤ እያሉ እየተሸከረከሩ እጅግ መጠኑ ከፍተኛ የህዝብ ሀብት እያባከኑ ከ15 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በርሀብና በችጋር እያለቀ መሆኑን ዲፕሎማቶች ቢገልፁላቸውም አሁንም በያዙት ወልጋዳና ጠማማ ግትር ሀሳብ ቀጥለውበት «ከእኛ አቅም በላይ የተከሰተ ርሀብ በሀገሪቱ አልተፈጸመም »በማለት አስገራሚና አስደንጋጭ መልስ በመስጠታቸው ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የበርካታ ሀገር ዲፕሎማቶች ማዘናቸውን ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

ቀድሞ ከነበረው የረሀብተኛ ቁጥር በያዝነው ሳምንት እጅግ ያሻቀበ በመሆኑ አጣዳፊ እርዳታ እንደሚያስፈልገው የአለም ምግብ ፕሮግራም እየወተወተ ቢሆንም የወያኔ ባለስልጣናት ግን ለረሀብተኛ ወገኖቻችን ትኩረት ሳይሰጡ ጉባኤ እና ስብሰባ እያሉ መክረማቸው ዲፕሎማቶቹን እንዳስገረመም እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

ወትሮ ከነበረው የረሀብተኛ ቁጥር በከፋ ሁኔታ በተለይ በወሎ ፤ በሐረር፤ በሸዋ እና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ረሀብ በመከሰቱ ብዙ ሰዎች እየሞቱ መሆኑን

ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገልፆ ከአሁን በሁዋላ ያለው ወቅትም እጅግ አስቸጋሪ እንደሚሆንም ዘገባው አስረድቶዋል::

ህዝብ የዕለት ጉርስ ያለህ! አድኑኝ እያለ የድረሱልኝ ጥሪ እያሰማ ባለበት ወቅት የወያኔ ድልብ መሀይም ካድሬዎች ግን በየቀኑ ለየእያንዳንዳቸው ብዙ ሺህ ብር ተመድቦላቸው እየተሽከረከሩ ሲዝናኑ መታየታቸው ለሀገርና ለህዝብ ፀር መሆናቸውን ያረጋገጥንበት ነው ሲሉ አንድ የእድሜ ባለፀጋ የአዲስ አበባ ነዋሪ እንባ እየተናነቃቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በሌላ በኩል የወያኔ ቡድን በህዝቦች ላይ በሚያደርሰው በደልና ግፍ ምክንያት የተለያዩ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በቡድን እየሆኑ ዱር ቤት እያሉ  እየተፋለሙ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሱን ዘገባዎች ጠቆሙ::

በቅርቡ የጎንደርን መሬት ወያኔ ለሱዳን መሸጡን ተከትሎ በጎንደር ውስጥ ከፍተኛ ውጊያ መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልፆ በተለይም ወጣቱ በእልህና በቁጭት በወያኔ ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት እየሰነዘረ ጉዳት ያደረሰበት በመሆኑ ወያኔ በየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ እና በየተራራው ላይ ጦሩን አስፍሮ እንደሚገኝ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

በዚህ ውጥረት ውስጥ ያለው የወያኔ ጦር ነሐሴ 29 ቀን 2000 ዓ. ም. በሰሜን ጎንደር ታች አርማጭሆ ማሰሮ ደንብ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ አንድ የወረዳ አስተዳዳሪን  አጅበው በሚሄዱ ታጣቂዎች ላይ የወያኔ ወታደሮች ተኩስ ከፍተው 5 ታጣቂዎችን የገደሉ ሲሆን፤ ከወታደሮቹም 2 መገደላቸውን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

የወያኔ ግልገል ሹም የሆነውን የማይነጋት ወረዳ አስተዳዳሪን አጅበው ወደ ታች አርማጭሆ በመጉዋዝ ላይ የነበሩት ታጣቂዎች ሀገር ሰላም ነው ብለው በመጉዋዝ ላይ እንዳሉ በአካባቢው በስጋትና በፍርሀት ተወጥሮ የተቀመጠው የወያኔ ጦር የተቃዋሚ ታጣቂ መጣብኝ በማለት ሳያረጋግጥ ተኩስ ከፍቶ ከታጣቂዎቹም የተኩስ ምላሽ በመሰጠቱ እርስ በርስ ለሰዓታት ያህል ሲታኮሱ እንደነበርና ከሁለቱም ወገን 7 ሰዎች እንደሞቱና አስተዳዳሪውም የመቁሰል አደጋ እንደደረሰበት  ዘገባው አብራርቶዋል::

በጎንደር፣በጋምቤላ፣ በአሶሳ ፣እና በወለጋ ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቃዋሚ ታጣቂ ሀይሎች በወያኔ ወታደሮችና ፌዴራል ፖሊሶች ላይ ያልታሰበና ድንገተኛ ጥቃት እያደረሱ በመሆናቸው ስጋት ውስጥ የወደቁት የወያኔ ጄኔራሎች ወታደሮቻቸውን ሌት በጨለማ፣ ቀን በብርሀን እያንከራተቱዋቸው ከመሆናቸውም ባሻገር በቁርና በበረሀ እየጠበሱዋቸው በመሆኑ ከፍተኛ ምሬት እያሰሙ መሆኑንም ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ::

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጎንደር ውስጥ የተጠናከረ ኃይል ያለው የተቃዋሚ ታጣቂ አለ ተብሎ በመረጃ የተገደገፈ ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በመነገሩ እና የጦር አለቆቹም በመደንገጣቸው ሁለት

ክፍለ ጦር በአካባቢው እንዲሰፍር መደረጉን የገለፁት የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጦሩ በጎንደር ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ ሌሊት ለአሰሳ በሚል ሲንቀሳቀስ ብዙ ጊዜ እርስ በርስ ግጭት እየፈጠሩ በርካታ ወታደሮች ለሙትና ለቁስለኛነት እየተዳረጉ እንደሚገኙ ይኸው የምንጮቹ ጥቆማ ያስረዳል።

በቅርቡም በወረዳ አስተዳዳሪው እና በአጃቢዎቹ ላይ የደረሰው አደጋ በተመሳሳይ ሁኔታ ወታደሮቹ ስጋት ውስጥ በመሆናቸው በድንጋጤ በወሰዱት የተኩስ እሩምታ መሆኑን ያስረዱት ምንጮቹ የጎንደር ህዝብም በወያኔ ወታደሮች እንግልትና ወከባ ስለሚደርስበት ከፍተኛ ምሬት እያሰማ መሆኑን አስረድተዋል።

በወታደራዊና በሲቪል ተቋማት ላይ ከፍተኛ ችግር የገጠመው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን «አዲስ የአሰራር ለውጥ» በሚል በየመስሪያ ቤቱ ውስጥ አምስት አምስት ካድሬዎች መመደቡን ከተለያዩ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች የደረሱን ዘገባዎች ገለፁ።

ከመስከረም 1 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው ይኸው አዲሱ ምደባ ለየእያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት አምስት አምስት የህዝብ ግንኙነት ሠራተኛ ተብለው ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የተመረቁ የደህንነት ስራ የሚሰሩ ካድሬዎች መመደባቸውን የገለፀው የደረሰን ዘገባ እነዚህ ካድሬዎች የተመደቡት በህዝብ ግንኙነት ስም ይሁን እንጅ ስራቸው የተመደቡበትን መስሪያ ቤት ሰራተኞች ወሎና እንቅስቃሴ ለመከታተል መሆኑንም ዘገባው አጋልጦዋል።

EthioLion.com